Berhan International Research Journal of Science and Humanities (BIRJSH), 2026, 10(1), 113-124
*Journal homepage*: www.journals.dbu.et *ISSN: 2414-2794, eISSN: 3006-578X*

# Mental Disability and Power Relation In *Ibdu*

Getachew Tesfa[1], Ayele Fikre[1], and Kibour Engidawork[2]

1 Department of Amharic Literature and Folklore, Addis Ababa University, Addis Ababa, Ethiopia
2 Department of Sociology, Addis Ababa University, Addis Ababa, Ethiopia
*DOI: https://doi.org/10.61593/DBU.BIRJSH.01.10.08*

**Abstract**

Although disability has existed as a thematic concern in modern Amharic literature for at least sixty years, it has received disproportionately little critical attention relative to the overall volume of literary production. This study addresses this knowledge gap within Ethiopian literary scholarship. Grounded in the understanding that disability encompasses physical, sensory, and cognitive dimensions, this study examines the portrayal of mental disability in Awgichew Terefe's 2008 novel, Ibidu. Utilizing a first-person narrative point of view, the novel effectively exposes the protagonist's internal psyche and emotional state. Framed within Critical Disability Studies—a theoretical framework that remains largely underutilized in the Ethiopian literary tradition—this qualitative inquiry analyzes the complex relationship between identity and power relations. Through textual and thematic content analysis, the study demonstrates that mental disability is fundamentally represented as a form of acute powerlessness. The findings reveal that characters with mental illnesses are depicted as uniquely susceptible to discrimination, stigma, systemic abuse, and violence, often finding them pushed to the absolute margins of society and stripped of human dignity.

**Keywords**: Disability, Impairment, schizophrenia, Identity, Power relations
*Corresponding author email: getesfa2008@gmail.com
Article information: Received 16 March 2026; Revised on 24 May 2026; Accepted on 11 June 2026

**© 2026 Debre Berhan University. All rights reserved**

## አእምሯዊ አካል ጉዳተኛነትና የኃይል ግንኙነት በ*እብዱ* ልቦለድ ውስጥ

በጌታቸው ተስፋ[1]፣ አየለ ፍቅሬ[1]፣ እና ክቡር እንግዳ ወርቅ[2]
[1] የአማርኛ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
[2] የሥነ ማኅበረሰብ፣ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

**አጽህሮተ ጥናት**

በዘመናዊው የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ አካል ጉዳተኛነት ጉዳይ ከሆነ ቢያንስ የስድስት አሠርት ዓመታት ዕድሜ ያስቆጠረ ቢሆንም፣ እንደ ሥነ ጽሑፍ ምርቱ መበራከትና ከአጠቃላዩ የሕዝብ ብዛት ውስጥ ስነት ያለባቸው ወገኖች ቁጥር ካለው ድርሻ አኳያ ተገቢ ትኩረት አግኝቷል ለማለት አያስደፍርም። የዚህ ጥናት ዋነኛ አነሳሽ ምክንያትም በአገራችን ልቦለዶች ውስጥ የአካል ጉዳተኛነት አስተማስሎ (Representation) በበቂ አለመጠናቱ የፈጠረውን የዕውቀት ክፍተት መሙላት ነው። ጥናቱ የአእምሯዊ አካል ጉዳተኛነት አስተማስሎን ከኃይል ግንኙነት አኳያ በአውግቸው ተረፈ *እብዱ* ልቦለድ ውስጥ የመመርመር ዓላማ አለው። ለዚህም ሒሳዊ የአካል ጉዳተኛነት ጥናትን የንድፈ ሐሳብ መሠረቱ አድርጎ ማንነትንና የኃይል ግንኙነትን በጭብጥነት ይዞ የይዘት ትንተናን ጥቅም ላይ አውሏል። ጥናቱ ለአገራችን ሥነ ጽሑፍ እንግዳ የሆነውን ሒሳዊ የአካል ጉዳተኛነት ጥናት የማስተዋወቅ ፋይዳም ይኖረዋል። ለጥናቱ የተመረጠው *እብዱ* ልቦለድ በ2002 ለንባብ የበቃ ሲሆን፣ የአእምሮ ጤናን ችግር ከራሱ ከገጸ ባህርይው በመነጨ ትረካ (አንደኛ መደብ) የቀረበ በመሆኑ የሕመምተኛውን ውስጣዊ ስሜት ገላልጦ የማሳየት አንጻራዊ ተጨባጭነት አለው። አእምሯዊ አካል ጉዳተኛነት ከሌሎቹ የአካል ጉዳት ዓይነቶች ሁሉ ይበልጥ ለአድልኦ፣ መገለልና ጥቃት የሚጋለጥበት እና የኃይል አልባነት ገጽታ የሚስተዋልበት መሆኑ በዚህ ልቦለድ ውስጥም በተደጋጋሚ የሚታይ እውነታ ነው። የአእምሮ ጤና ችግር ለልማዳዊው የጅምላ ፍረጃ የተጋለጠበት፣

የጭካኔ፣ የሰብአዊ ባህርይ መንጠፍ ችግርና የጉስቁልና ገጽታዎች ጎልተው የቀረቡበት ልቦለድ ነው። በአጠቃላይም አካል ጉዳተኛነት ኃይል አልባ ሆኖ በሌሎች የሕይወት ዕጣ ፈንታው የሚወሰንበት፣ በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ሕልውናው ለወለፈንዴነት የተጋለጠበት፣ እንደአንድ ማኅበራዊ ቡድን የጥቃት ዒላማ የሆነበት፣ ከሕይወት ጠርዝ ተገፍቶ ከሞት የሚነጻጸርበትና ከሰብአዊ ፍጡር ክብሩ ወርዶ የእንስሳ ተፈጥሮን የሚጋራበት እውነታ ገዝፎ ታይቷል የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል።

**ቁልፍ ቃላት፡** ማንነት፣ አካል ጉዳተኛነት፣ አካላዊ ስነት፣ “እብድነት”፣ የኃይል ግንኙነት

## መግቢያ

በተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል ላይ እንደሚያነጣጥሩት ሕዳጣን ተኮር ጥናቶች (Minority Studies)፣ ማለትም እንደአንስታይ ሒስ (feminist)፣ የዘረኛነት ሒሳዊ ጥናት (critical race) እና የተመሳሳይ ፆታ (queer) የሥነ ጽሑፍና የባህል ጥናት ስልቶች ሁሉ የአካል ጉዳተኛነት ጥናትም በአንድ በተወሰነ ቡድን ላይ ያነጣጥራል። ይኸውም ከዓለማችን ሕዝብ 16 በመቶ የሚሆነውን ቁጥር የሚይዙትና በበሰ ድህነት ውስጥ የሚገኙ ያልበቁ (disempowered) የኅብረተሰብ ክፍሎችን (አካል ጉዳተኞችን) ይመለከታል። የአካል ጉዳተኛነት ጥናት በ20ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ በምዕራቡ ዓለም የተቀሰቀሱትን የአካል ጉዳተኛነት መብቶች ንቅናቄ ተከትሎ የፈለቀ መስክ ነው (Hall, 2016)። የመብት ንቅናቄዎቹን መሳካት ተከትሎ Erving Goffman እና Michel Foucaultን የመሳሰሉ ጸሐፊዎች ያቀረቧቸው ማንነትን መሠረት ያደረጉ በይነ ዲሲፕሊናዊ የጥናት መጣጥፎች የሰብአዊነት ጥናት መስኮችን የእይታ አቅጣጫ ያስቀየሩ ሆነው ለጥናቱ መጀመር መንገድ ጠራጊ ሆነዋል። በዚህም መሠረት የአካል ጉዳተኛነት ጥናት መሠረቱ “አካል ጉዳተኛነት ማለት ስነትን ተገን በማድረግ የሚቃጣ የተቀናጀ የማግለል ድርጊት (ሥርዓት) ነው” (Hall, 2016፣ Singh, 2015፣ Nasrullah, 2018) በሚል ብያኔ ላይ ያተኮረ ነው። ይህም ማለት ስነት የአካል ብልት የተለመደ ሥነ ሕይወታዊ ተግባሩን ያለማከናወን ችግር እንጂ “አለመቻል” (Disabling) አይደለም። አካላዊ ስነት ያለባቸው ሰዎች “ጤነኛ” ተብለው ከሚታወቁት ሰዎች እኩል መግባባት፣ መሥራትና ማናቸውንም ማኅበራዊ ተሳትፎ ማድረግ እየቻሉ ማኅበራዊ ሥሪት በሆነው ፍረጃ አካል ጉዳተኛ (Disabled) መደረጋቸው የዚህ የጥናት መስክ ዋነኛ ትኩረት ነው።

በዘመናዊው የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ በጉዳይነት ከተነሳ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ዕድሜ ያስቆጠረው አካል ጉዳተኛነት እንደስነ ጽሑፍ ምርቱ መበራከትና ከአጠቃላዩ የሕዝብ ቁጥር ውስጥ ስነት ያለባቸው ወገኖች ቁጥር ካለው ድርሻ አኳያ ተገቢ ትኩረት አግኝቷል ለማለት አያስደፍርም። ዘመናዊው የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ከተጀመረበት ከ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ አንስቶ ለንባብ የበቁት የአማርኛ ልቦለዶች አካል ጉዳተኛነትን ርዕሰ ጉዳያቸው አድርገው አንድም በጭብጥነት፣ አለያም በገጸ ባሕርያት ቀረጻ የተጠቀሙ ልቦለዶች ከሃያ እንዳልበለጡ በቤተ መጻሕፍት ፍለጋና ከደራስያንና የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች ጋር በተረገ ውይይትና የጋራ ፍለጋ ለመረዳት ተችሏል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ አካል ጉዳተኛነት በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ በበቂ ሁኔታ አልተጠናም ማለት ይቻላል። በቤተ መጻሕፍት ፍተሻ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የተሠሩ ሦስት የሁለተኛ ዲግሪ ጥናቶችን ያገኘሁ ሲሆን፣ ሦስቱም ከስነት ዓይነቶች መካከል የአዕምሮ ጤና ችግርን የተመለከቱ ናቸው። ቀሪዎቹ ሁለቱ የስነት ዓይነቶች፣ ማለትም ሕዋሳዊና አካላዊ ስነቶች ምንም ትኩረት አላገኙም ማለት ነው። ሦስቱ ጥናቶች ከእንግሊዝኛ ሥነ ጽሑፍ፣ ከልዩ ፍላጎት ትምህርትና ከሥነ ልቡና ትምህርት ክፍሎች የተገኙ መሆናቸውም የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ አጥኚዎች ለጉዳዩ ትኩረት መንፈጋቸውን ሊያመለክት ይችላል። በእንግሊዝኛ ሥነ ጽሑፍ የተሠራው ጥናት በአውግቸው ተረፈ እብዱ ላይ ያተኮረና በቋንቋ አጠቃቀሙ ላይ ተመሥርቶ ሥነ ልሣናዊ፣ አዕምሮታዊ ሥነ ሥልትና ንባበ አእምሮን በመፈከሪያ መሣሪያነት የተጠቀመ ሲሆን፣ የገጸ ባህርይው የቃላት ምርጫና የሥነ ፍቺ ዝንባሌ የአእምሮ ጤና ችግር እንዳለበት የሚያላክት መሆኑን አሳይቷል። ቀሪዎቹ ሁለት ጥናቶች ደግሞ በአማርኛ ፊልሞች ላይ ትኩረት አድርገው የኦቲዝምና ስኪዞፍሬኒያ ችግሮች በፊልሞቹ ውስጥ የቀረቡባቸውን ሁኔታዎች ፈትሸው ደራሲዎቹ ስለአዕምሮ ጤና ችግር ያላቸው ግንዛቤ ደካማ መሆኑን በድምዳሜያቸው አሳይተዋል። ምንም እንኳ ጥናቶቹ በአእምሮ ጤና ስነት ላይ የተመሠረቱ ቢሆኑም፣ የአካል ጉዳተኛነት ማኅበራዊ ሥሪትን ያልተመለከቱ በመሆናቸው የእኔን ሙከራ የተለየ ያደርገዋል።

በዚህም መሠረት አካል ጉዳተኛነት የአካል ጉዳት ሳይሆን ጉዳቱን (ስነቱን) ተንተርሶ በማኅበረሰቡ የሚፈጸም የተቀናጀ ጥቃትና ፍረጃ ወይም ማኅበራዊ ሥሪት (Social Construct) እንደመሆኑ ይህን መሪ የአካል ጉዳተኛነት ጥናት ጽንሰ ሐሳብና ሞዴል ይዞ የተነሳ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ጥናት አለመኖሩ የሚፈጥረውን የዕውቀት ክፍተት መሙላት የጥናቱ ዓቢይ አነሳሽ ምክንያት ነው። በተጨማሪም ሒሳዊ የአካል ጉዳተኛነት ጥናት ለአገራችን የሥነ ጽሑፍ ጥናት

አንጻራዊ አዲስነት ያለው በመሆኑ የጥናት መስኩን በመጠኑም ቢሆን ለማስተዋወቅ መነሳቴ ተጨማሪ ምክንያት ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል። በዚህ መነሻነትም ጥናቱ "እብድ" ምን ዓይነት "ሰው" ነው? በማኅበረሰብ ውስጥ ያለው አቀባበልና ማንነት ምን ይመስላል? ምን መገለጫዎችስ አሉት? በሚሉ የጥናት ጥያቄዎች የሚመራ ይሆናል።

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ አካል ጉዳተኛነት በማኅበረሰብ የኃይል ግንኙነት ውስጥ ያለውን ሥፍራ በእብዱ ልቦለድ አስረጂነት መመርመር ነው። በተጨማሪም ጥናቱ የ"እብደት"ን ማኅበራዊ አቀባበል ከአገራችን ዐውድ አኳያ መፈተሽ፣ በልቦለዱ ውስጥ የተገለጹ ማኅበረሰብ ሠራሽ የ"እብደት" መገለጫዎችን ማሳየት እና የእብደትን ማኅበራዊ ሥፍራ ወይም ማንነት መመርመር የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎች አሉት። ለዚህም ሒሳዊ የአካል ጉዳተኛነት ጥናትን የንድፈ ሐሳብ መሠረቱ አድርጎ ምንባባዊ ትንተናን በመጠቀም ማንነትንና የኃይል ግንኙነትን ጭብጥ በማድረግ ይተነትናል። ጥናቱ ለአገራችን ሥነ ጽሑፍ እንግዳ የሆነውን ሒሳዊ የአካል ጉዳተኛነት ጥናት የማስተዋወቅ ፋይዳም ይኖረዋል።

ለዚህ ጥናት የተመረጠው *እብዱ* ልቦለድ የታተመው በ2002 ዓ.ም ነው። ደራሲው አውግቸው ተረፈ በአገራችን ሥነ ጽሑፍ ውስጥ በ1970ዎቹ ወደ መድረክ ከመጡ ደራስያን አንዱ ነው። የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው እብዱ የተሰኘው ልቦለዱ በ1970ዎቹ መጨረሻ ያጋጠመውን የአእምሮ ጤና ችግር መነሻ አድርጎ የጻፈው ሲሆን፣ ቀደም ሲልም ከጻፋቸው አጫጭር ልቦለዶች አብዛኞቹ የአእምሮ ጤና ችግር ያለባቸው ገጸ ባህርያት ያላቸው ነበሩ። ልቦለዱ ለዚህ ጥናት የተመረጠው የደራሲው የሕይወት ልምድ የቀረበበት በመሆኑ ተጨባጭነቱ ብልጫ ተሰጥቶት ነው።

## አካል ጉዳተኛነት እንደማንነት

የአካል ጉዳተኛነት ጥናት አካል ጉዳተኛነትን እንደማኅበራዊና ፖለቲካዊ ክስተት (እውነታ) መመልከቱ ምናልባትም ልዩና አክራሪ አዝማሚያ ያለው ሆኖ እንዲታሰብ አድርጎታል። አካል ጉዳተኛነትን በአንድ ሰው አካል ላይ እንደተወሰነ የጤና ችግር ለሚመለከቱ ወገኖች (ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ የብዙኃን ዕይታ ነው) ይህን መሰሉ ስልት አስገራሚ ሊሆን ይችላል (Nasrullah, 2018)። ይሁንና የአካል ጉዳተኛነት አጥኚዎች እንደሚጠቁሙት "የጤና ሞዴል" አካል ጉዳተኞችን የተጎዱ፣ የበታች፣ ተሐድሶና ፈውስ የሚያስፈልጋቸው አድርጎ በማቅረብ አሉታዊ ትርጉምን እያሳደረ የአድልኦ ሰለባ ያደርጋቸዋል። ሕክምና ለአካል ጉዳተኞች አስፈላጊ መሆኑ ባይካድም የጤና ሞዴል ግን አጠቃላይ ስዕሉን የሳተ ዕይታ አለው። በአንጻሩ አካል ጉዳተኛነት ከአካላዊ ሁኔታዎች ይልቅ በባህላዊና አካባቢያዊ ምክንያቶች የሚፈጠር ነው ሲሉ ይሞግታሉ፤ ትኩረታቸውንም እዚያ ላይ ያደርጋሉ (ዝኒ ከማሁ)። የአካል ጉዳተኛነት ጥናት ፈር ቀዳጆች ለ"ማኅበራዊ ሞዴል" ልባቸው ክፍት ሲሆን፣ ማኅበረሰብ አካል ጉዳተኛ ሰዎችን የሚያስተናግድበትን ሁኔታ መመልከትን ምርጫቸው አድርገዋል። ይህን መሰሉ ስልትም የመብት ተኮር ማንነት መስኮች አቻዎች አሉት። ለምሳሌ በ1952 (እ.ኤ.አ.) የአንስታይነት አቀንቃኟ Simone de Beauvoir የጻፉት ተጠቃሽ አባባል "ሴትነት የሚወለዱት ሳይሆን የሚሆኑት ነው" ("one is not born, but rather becomes, a woman") ሥነ ሕይወት ሳይሆን ባህል ሴት የመሆንን ትርጉም የሚወስን፣ የሚፈጥር መሆኑን ያመለክታል (Beauvoir 1952: 247)። ይህ ጥቅስ አካል ጉዳተኛነት ማኅበራዊ ሥሪት እንጂ በአካል ስንት ምክንያት የሚከሰት የግለሰቡ የአለመቻል ችግር እንዳልሆነ የሚያስገነዝብ አንድምታ አለው። አካል ጉዳተኛነትን ጨምሮ ያልበቁ ቡድኖች ከተጨባጭ አካላዊ ጉድለቶች ይልቅ ማኅበረሰቡ በኢፍትሐዊነት እንደሚያስተናግዳቸው Beauvoir ይጠቁማሉ።

ለአካል ጉዳተኛነት ጥናት መስክ እንደማኒፌስቶ በሚቆጠረው መጽሐፋቸው Claiming Disability (1998) Simi Linton የማኅበራዊ ሞዴልን ትሩፋቶች አጠቃለው አቅርበዋል። በቅድሚያ አካል ጉዳተኛነት ዓይነተ ብዙና ልዩነቱም ሰፊ ቢሆንም በመካከላቸው አሰባሳቢ ማንነት ሆኖ ማገልገሉ ይጠቀሳል። የዕይታ ስንት ያለባቸው፣ የአዕምሮ ጤና ጉዳት ያለባቸውና ተሽከርካሪ ወንበር የሚጠቀሙ ሰዎች የጋራ የሚያደርጋቸው ምን አሰባሳቢ ነገር ይኖራል?

አብዛኞቹ የአካል ጉዳተኛነት የፍትሐ ብሔር መብት ሕጎችና ተነሳሽነቶች እነዚህን ልዩነቶች ጥቅም ላይ ያውሏቸዋል (ይመለከቷቸዋል)። በ1990 (እ.ኤ.አ.) የወጣው የአሜሪካ የአካል ጉዳተኛነት ሕግ (The Americans' Disabilities Act of 1990 (ADA)) አካል ጉዳተኛነትን የሚበይነው "አንድን ወይም ከዚያ በላይ የሆነን ዓቢይ የሕይወት ተግባር በቋሚነት የሚያውክ አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ስንት" ወይም የተመዘገበ (የሚታይ) ስንት ብሎ ብቻ ሳይሆን፣ "ይህን መሰሉ ስንት እንዳለበት መቆጠርንም" ይጨምራል። ይህም ማለት ማኅበራዊ አተያይና አረዳድ አካል ጉዳተኛነትን የሚፈጥር መሆኑ ያመለክታል። ይበልጥ ግልጽነት ያለው በ2008 የወጣው የተባበሩት መንግሥታት የአካል ጉዳተኛ ሰዎች መብቶች ድንጋጌ (United Nations Convention on the Rights of Persons with Disabilities) ደግሞ "ስንት

ያላቸው ሰዎች ከሌሎች ጋር እኩልና ውጤታማ ማኅበረሰባዊ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ከሚጋረጡባቸው የአስተሳሰብና የአካባቢያዊ ገደቦች (ከለላዎች) ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት (መስተጋብር) ነው" ይላል። እነዚህ ምሳሌዎች አካል ጉዳተኛነት የማህበራዊ ከባቢያዊ ሁኔታና የአካል ጉድለት ጥምራ ውጤት ሆኖ በዓለማቀፍ ደረጃ ግንዛቤ እያገኘ መሄዱን ያስረዳሉ።

የአካል ጉዳተኛነት መብት ተሟጋቾች እና አጥኚዎች ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኛነት እሳቤን ለማምጣት ይታገላሉ። ምክንያቱም በአካል ጉዳተኛነት ዙሪያ የሰፈነው አድልኦ በሁሉም አካባቢዎች ባሉ ባህሎች ውስጥ ጽኑእ የአፍራሽነት ገጽታ አለው (Nasrullah, 2018)። ወጥ የሆነ የአካል ጉዳተኛነት አረዳድ እንዳይኖር ያደረገው አንደኛው ችግር በሕግ አካል ጉዳተኛ የተባሉ አንዳንድ ሰዎች የአካል ጉዳተኛነት ደረጃቸውን ለመቀበል አለመፍቀዳቸው ነው። ለምሳሌ በሚኖሩበት ባህል መስማት የተሳናቸው ተብለው የሚታወቁ ሰዎች የምልክት ቋንቋ ተጠቃሚ በመሆናቸው ምክንያት የኩሩ ሥነ ልሳናዊ ንዑሳን አድርገው ራሳቸውን የሚቆጥሩ ይሆናሉ፤ በአንጻሩ የምልክት ቋንቋ ተጠቃሚ የሆኑ ሌሎች መስማት የተሳናቸው ሰዎች ደግሞ የሚገጥሟቸውን ማኅበረሰባዊ መሰናክሎች ግምት ውስጥ አስገብተው ሁለቱንም ጫፍ (የደህነኛነትና የአካል ጉዳተኛነት ተቃርኖ) ይይዛሉ። የ"ድንክ" ማኅበረሰብ አባል የሆኑ ጥቂት ሰዎች ራሳቸውን እንደአካል ጉዳተኛ የማይቆጥሩ ሲሆን፣ በቅርብ እንደአካል ጉዳተኛ መፈረጅ የጀመሩ ወገኖችም ይህን ሁኔታ ለመቀበል ይቸገራሉ።

ሁለተኛው ገደብ ደግሞ በአካል ጉዳተኛነት ማኅበረሰብም ሆነ በአካል ጉዳተኛነት ጥናት ውስጥ የሚታይ የክብር ተዋረዳዊ አዝማሚያ ነው። ነጭ አካል ጉዳተኞች ከሕዳጣን ዘር አካል ጉዳተኞች የበለጠ ትኩረት ማግኘታቸው የተለመደ ነው ወይም ተሽከርካሪ ወንበር ተጠቃሚ አካል ጉዳተኞች ከአዕምሮ ጤና ጉዳተኞች የበለጠ ግምት ያገኛሉ (ዝኒ ከማኹ)። በርግጥ በዚህ ረገድ የሚታየው ያልተመጣጠነ የክብር ተዋረድ መሻሻል እየታየበት ቢሆንም ብዙ ሥራ የሚፈልግ ይመስላል።

የመጨረሻው መሰናክል ደግሞ የአካል ጉዳተኛነት ማንነት እንደአንድ ራሱን የቻለ ምድብ የተረጋጋ አለመሆኑ ነው። የአካል ጉዳተኛነት ድንበሩ አወዛጋቢ ነው። በተለይም ጊዜያዊ፣ የማይታይ ወይም በመድኃኒት የሚድን የጉዳት ዓይነት በሚሆንበት ጊዜ ይበልጥ አደናጋሪ ይሆናል። (Davidson 2016: 434) ከዚያ ውጪ ግን Irving Zola እንደሚሉት አካል ጉዳተኛነት ዓለማቀፍ እውነታ (ልምድ) ነው። (Shakespeare 2006: 204) ምክንያቱም በድንገት ካልሞትን በስተቀር በሕይወታችን የሆነ ነጥብ ላይ አካል ጉዳተኛ ልንሆን ስለምንችል ነው። የአካል ጉዳተኛነት ንቅናቄ አልፎ አልፎ የሚጠቀምበት አሽሙራዊ ሐረግ "ጊዜያዊ ቻይ አካል" ("TAB" for "temporarily able-bodied") አካል ጉዳተኛ ያልሆኑ "ጤነኛ" ሰዎችን መግለጫ ነው። የአካል ጉዳተኛነት ጥናት እንደሚያስገነዝበንም ማንም ሰው አካል ጉዳተኞች በሚስተናገዱበት ሁኔታ ውስጥ ድርሻ አለው።

የአካል ጉዳተኛነት ዓለማቀፋዊ የመሆን ዕድል አልፎ አልፎ ምሁራንን ሲከፋፍል ይታያል። አካል ጉዳተኛነት የትኛውንም የማንነት ምሥረታ እስከነካ ድረስ እንደሥርዓተ ጾታ፣ ዘር፣ መደብ፣ ጾታዊነት የመሳሰሉ ማንነቶችን አቅፎ የሚይዝ አውራ ማንነት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል ሲሉ Lennard J. Davis (2002) ይሞግታሉ። ከዚህ ሐሳብ በተቃራኒው የሚቆሙት Linton (1998) ደግሞ አካል ጉዳተኞች ዝቅተኛ ግምት ተሰጥቷቸው እስከተገለሉ ድረስና በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚስተናገዱበትን አስከፊ ሁኔታ ለመግለጽ ስያሜው እስካገለገለ ድረስ በአካል ጉዳተኛና ጉዳተኛ ባልሆኑ ሰዎች መካከል የተዘረጋውን መስመር ማጥፋትን አልቀበለውም ይላሉ። የአካል ጉዳተኛነት ማንነትን አለመርጋት የሚቀበሉት Siebers በግልጽ የተወሰነ የአካል ጉዳተኛነት ማኅበረሰብና የህዳጣንነት ማንነት የፖለቲካ ጥቅም አለው ይላሉ።

እነዚህ ጉዳዮች በአካል ጉዳተኛነት ምሁራን ሥነ ጽሑፋዊና የባህል ትንተና ውስጥ የሚዘወተሩ ናቸው። በ1980ዎቹ የአካል ጉዳተኛነት ጥናት በማኅበራዊ ሳይንስ የጥናት ስልቶች ተፅዕኖ ሥር የነበረ ሲሆን በ1990ዎቹ ደግሞ የሥነ ጽሑፍና የባህል ሒስ መሪነቱን ይዟል። የሥነ ጽሑፍ ሊቃውንት የማንነትና የሥነ ውበት እሳቤን በማስረጽ ብቻ ሳይወሰኑ ማኅበራዊ አተያይን፣ ሥነ ምግባርንና ሰብአዊ መብቶችን በመቅረጽ ጭምር የጥናት መስኩን ጉልህ አድርገውታል። (Hall 2016: 53) በሂደቱም አካል ጉዳተኛነት ማዕከላዊ እና ተንታኝ የሒስ ምድብ እንዲሆን አስችለውታል።

ሒሳዊ የአካል ጉዳተኛነት ንድፈ ሐሳብ ከማንነት ሥነ ጽሑፍ ቤተሰብ ጋር ሊያያዝ ይችላል። የአባላቱ አንዳንድ መለያ ባህርያት ሥነ ጽሑፍ ያንን ማንነት በሚጋሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ላይ የሚኖረውን የተፅዕኖ ልክ ለማጥናት እንደ ማደራጃ መርህ ሆኖ ያገለግላል። የማንነት ሥነ ጸሑፍ/ ሒስ የሚመነጨው ከማንነት ማኅበራዊ እሳቤ ሲሆን ስሙ እንደሚያመለክተው በማህበራዊ ማንነት ዙሪያ የተዋቀረ የሥነ ጽሑፍ አዝማሚያ ነው። ማንነትን መሰረት ባደረገ የሥነ ጽሑፍ መስክ ውስጥ ካሉት አደጋዎች አንዱ የቡድኑ

ማንነት የሚወሰንበት ሁኔታ እምቅ አባላትን (አባል ሊሆኑ የሚችሉ ብቁ ወገኖችን ሳይቀር) የማግለል፣ የቡድን ርዕዮተ ዓለምን እንዲከተሉ የመጠየቅ እና በቡድኑ ውስጥ ያሉ ልዩነቶች (ብዝሃነት) እንዲጠፉ ማድረግ ነው።

### የኃይል ግንኙነት

Michel Foucault ሥልጣን ወይም ኃይል በማናቸውም ሰብአዊና ተቋማዊ ግንኙነት ውስጥ የሚታይ ተለዋዋጭ አቅም እንጂ የባርያና ጌታ መሰል ግንኙነት የሚወሰንበት የጉልበት ተዋረድ አይደለም ይላሉ (Foucault, 1980, 1978)፡ ፡ ሥልጣን ወይም ኃይል ከአንድ የተወሰነ ሥፍራ የሚመነጭ፣ በተወሰነ ግለሰብ ወይም ቡድን የበላይነት የሚያዝ ሳይሆን በማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ በተፈራራቂነት የሚገለጽ ሚና ነው። የFoucault የኃይል እሳቤ ሁለት ገጽታዎች እንዳሉት Kelly (2009) ያመለክታሉ፡ ፡ የመጀመሪያውና በጉልህነቱ የሚታወቀው ኃይል ሥርዓት መሆኑ ነው፤ ማለትም ሁሉንም ማኅበረሰብ የሚያቅፍ የግንኙነት መዋቅር ነው። ሌላው ደግሞ ግለሰቦች ወይም ተቋማት የኃይል (የሥልጣን) ባለቤቶች ሳይሆኑ ኃይልና ተቋቁሞ (power and resistance) የሚመነጩባቸው ማዕከላት የሚሆኑበት እሳቤ ነው። በዚህም መሠረት በሁሉም ማኅበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ ኃይል ሊመነጭ ሲችል ይህም ቤተሰብ፣ መንግሥታዊ የሥልጣን እርከን ወይም ሌሎች ማኅበራዊ ተቋማት የሚፈጥሩት ግንኙነት መሆኑ ልዩነት አያመጣም። ሁሉም ማኅበራዊ ተራክቦዎች የኃይል ግንኙነት ናቸው። ኃይል ጥቅም ላይ የሚውለው የተጠቃሚውን ዓላማ፣ ፍላጎትና ፈቃድ ተከትሎ ሲሆን ኃይል ባለበት ምንጊዜም ተቋቁሞ አለ። በመሆኑም ኃይል በተፈጥሮ ባህርይው አሉታዊ፣ ጨቋኝና አስገዳጅ ሆኖ ከፈቃዳችን ውጪ አንዳች ተግባር እንድናከናውን የሚገፋን አይደለም። ይልቁንም የአንድን ሥርዓት አካሄድ ተከትለን ራሳችንን ለደንቡ እንድናስገዛ ወይም በዚያ ሥርዓት ተጎጂ እንድንሆን የምንወስደው ምርጫ ሊሆን ይችላል (Gaventa, 2003)። በመሆኑም ኃይል የግለሰቦችን ታዛዥነት በተጽዕኖ አያመጣም።

በአንጻሩ ኃይል በሰብአዊ ግንኙነት ውስጥ የተጽዕኖና ተቋቁሞ ጉድኝት የማይለየው አስፈላጊና ገንቢ እውነታ ነው። በኃይልና ተቋቁሞ መካከል ያለው ያለመነጣጠል እውነታ በግለሰቦች መካከል ያለውን የኃይል ግንኙነት የጨቋኝና ተጨቋኝ ተለምዷዊ ገጽታ አያላብሰውም። ከዚያ ይልቅ ግለሰቡ ራሱን እንዲሠራ ገንቢ ሚና ይኖረዋል። ኃይል ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመነጭና ለተለያዩ ተግባራት የሚውል በመሆኑ በግንኙነቶች የማያቋርጥ የለውጥ ሒደት ውስጥ ይኖራል። በልኂቃን የተያዘ ኃይል በማኅበረሰብ ውስጥ ከላይ ወደ ታች ያለ የግንኙነት ቅጥ ሲኖረው በዝቅተኛው የኅብረተሰብ ክፍል የተያዘ ኃይል በበኩሉ በምላሽ ሰጪነት፣ በተቋቁሞ፣ በተቃውሞና ቅሬታ መልክ የሚገለጽ ሆኖ ይከሰታል (Van Dijk, 1993)። ይህ የግለሰቦች የኃይል ግንኙነት ማኅበራዊ መልክ እየያዘ ያድጋል።

### የአእምሮ ጤና ስነት

የአካል ጉዳተኛነት ጥናት ወደ መድረክ ካመጣቸው ንዑሳን የጥናት መስኮች መካከል አንዱ የሆነው የእብደት ጥናት (mad studies) ከ2008 ወዲህ ነው እግሩን የተከለው። ከዚያ በፊት ግን በአእምሮ ጤና ችግር ውስጥ ያለፉና ገጠመኞቻቸውን ተንተርሰው ጥናቶች ያበረከቱ ባለሙያዎች እንዳሳዩት የሕክምናው ስልት፣ ማኅበራዊ መገለሉ፣ እንደሰብአዊ ፍጡር አለመታየቱ፣ ወ.ዘ.ተ. ጉዳተኛውን ወደ ሞት የሚገፋ፣ በራሱ ዓለም እንዲወሰን የሚያስገድድና ጤናው ተመልሶለትም የመኖር ዋስትና የሚያጣበት ነው። በዚህ ረገድ Beresford እና Peter Campbell በDonaldson ውስጥ እንዲህ ያሉትን መጥቀስ ይቻላል፤ “A mental illness diagnosis…, although sometimes helpful in easing confusion and distress, effectively marks out the individual as a citizen of lesser value … isolated, distrusted, largely unemployed and dependent on the welfare system” (Donaldson, 2018: 14). በርግጥ የእብደት ጥናትና የአካል ጉዳተኛነት ጥናት ጎን ለጎን ሲደረጉ ኖሩ በመሆናቸው አንዱ የሌላው ተዋራሽ ወይም ንዑስ አድርጎ በመረዳት ረገድ ልዩነቶች ነበሩ። እንደ Margaret Price፣ Katie Aubrecht እና A.J. Withers የመሳሰሉ ከአእምሮ ሕመም አገግመው ዘርፉን ያጠኑ ባለሙያዎች ራሳቸውን እንደአካል ጉዳተኛ ካለመቁጠራቸውም በላይ በእብደትና በአካል ጉዳተኛነት መካከል ልዩነት አለ የሚለውን ጥያቄ መልስ አልባ አድርገውታል። በአካል ጉዳተኛነት ማዕቀፍ ውስጥም የእርከን ልዩነት እየተፈጠረ ባለ ዊልቼሩ ከዓይነ ስውሩ ጋር ባንድ መደመርን ሲፀየፍ፣ መስማት የተሳነው ከባለ ልምሻው እኩል መቆጠርን ሲሸሽ መታየቱ የተለመደ መሆኑን Donaldson ይገልጻሉ (2018፡ 14)። ከአካል ጉዳተኛነት ማኅበረሰብ ውስጥ አእምሯዊ አካል ጉዳተኛነት ዝቅ ያለ ግምት የሚሰጠውና የመገፋት ዕጣ ያለበት ንዑስ ምድብ ነው (ዝኒ ከማሁ፤ 17)።

በአገራችን የአእምሮ ጤና ችግር በአመዛኙ “እብደት” በሚል የወል ስያሜ የሚገለጽ በመሆኑ አስፈሪ፣ ከሰብአዊ ባህርይ የራቀና ጥቃት አድራሽ አድርጎ ባህሉ ይቀበለዋል። ምናልባትም “ወፈፌ”፣ “ንክ” እና “ጅል” የሚሉ የማለዘቢያ መጠሪያዎች ከመኖራቸው ውጪ ሁሉንም የጤና ችግር በአንድ ቋት ውስጥ የሚያስገባ ግንዛቤ ያለ ይመስላል።

የመዝገበ ቃላት ፍቺውን ብንመለከት ኪዳነ ወልድ “አቢድ፤ ዶት፤ (አብደ፣ የአብድ፣ ይእበድ፤ ዕብ፣ አባድ)፡- ማበድ፣ መቈጣት፣ አእምሮ ማጣት፣ መወግሸት፣ መነሣሣት፣ አፈፍ አፈፍ፣ ወፈፍ ወፈፍ ማለት፣ መስነፍ፣ ሞኝ አላዋቂ መሆን፣ መጥፋት፣ መበላሸት የልብ የናላ” (1948፤ 197) ሲሉ ይተረጉሙታል ። ደስታ በበኩላቸው፣ “አበደ፤ (አቢድ፣ አብደ)፡- በቁሙ ጮኸ፣ ተቈጣ፣ አእምሮ ዐጣ፣ ተሟረ፣ ላባና ሰሪቱ በራሱ ሻጠ፣ ወገሸ፣ ተነሣሣ፣ አፈፍ አፈፍ አለ፣ ወፈፈ፣ ጠፋ፣ ተበላሸ፣ ልቡ ናላው ዞረ፣ ራሱ ዞረ፣ ከስካርና ከበሽታ ካስማት ከመዳኒት የተነሣ ልብሱን ጣለ፣ ሮጠ፣ ፈረጠጠ” (1962፤ 74) ይላሉ። ምንም እንኳ ሁለቱም የሕክምና መዝገበ ቃላት ባለመሆናቸው የአእምሮ ሕመምን ትክክለኛ ፍቺ እንዲያስቀምጡ ባይጠበቅም የማኅበረ ባህላዊውን አረዳድ መጠቆማቸው አይቀርም። የዚህ አተረጓጎም ችግር ምናልባትም የአእምሮ ጤና ስነት ዓይነተ ብዙነት የፈጠረው ሊሆን ይችላል።  ይሁንና ማኅበረ ባህላዊው ግንዛቤያችን በእብደትና በወፈፌነት፣ በንክነትና በጅልነት ወይም በአእምሮ መቃወስና በርኩስ መንፈስ መጠቃት፣ ወዘተ መካከል ጉልህ ድንበር ሳያበጅ “እብድ” በሚል የወል ፍረጃ ላይ የቆመ ይመስላል።

የእብደት ዓይነተኛው ባህርይ የ”ሕልም ዓለም” መፍጠሩ ሳይሆን አይቀርም። Donaldson በአንስታይ ንቅናቄ ንቁ ተሳትፏቸው የሚታወቁትን Shulamith Firestoneን ልምድ በመጽሐፋቸው የመጀመሪያ ገጽ ላይ አቅርበዋል። Firestone በአእምሮ ጤና ችግር በተደጋጋሚ የሕክምና ተቋማትን የጎበኙ ሲሆን፣ በ1998 (እ.ኤ.አ.) ይህንኑ የአእምሮ ጤና ችግር ልምዳቸውን በጻፉበት Airless Spaces በተሰኘ መጽሐፋቸው በህልም ውስጥ መቆየታቸውን ይናገራሉ። በሚሰጥም መርከብ የላይኛው አካል ላይ ሆነው ከሞት ማምለጫ ፍለጋ ያደረጉትን ትንቅንቅ በመጽሐፋቸው ተርከዋል። መርከቡ በቤርሙዳ ትራያንግል አካባቢ ሲሰምጥ በመርከቡ የታችኛው ክፍል ውስጥ በሚገኝ ማቀዝቀዣ ፍሪጅ ውስጥ ተደብቀው ለማምለጥ ያደረጉትን ሙከራና መርከቡ እስኪገኝ በዚያው ለመቆየት ማሰባቸውን ያስቃኛል፡ ፡ በህልም ውስጥ መዋኘትና ቅዠት በሚመስል ዓለም ውስጥ የማሳለፍ እውነታ የብዙ አእምሯዊ አካል ጉዳተኞች ባህርይ ነው ይላሉ። (Donaldson, 2018: 1)

## አካል ጉዳተኛነት ማንነትና የኃይል ግንኙነት በእብዱ ልቦለድ ውስጥ (ትንታኔ)

የልቦለዱ ጭምቅ ታሪክ

በእብዱ ውስጥ የምናገኘው ታሪክ በሕልም ዓለም ውስጥ ሆኖ ከቁጥጥሩ ውጪ የሆነ ድርጊት የሚፈጽም ባለታሪክን ገጠመኝ ነው። ሕልም የወሲብ ግፊት ነጸብራቅ መሆኑን የሚያትተውን የፍሮይድን ንድፈ ሐሳብ አልቀበለውም፤ የቀን ገጠመኝ ተራዛሚ ግልባጭ መሆኑንም አላምንም ይላል ተራኪው። በሕልሙ ነቢይ እንደሆነ የተሰማው ባለታሪኩ፣ ዓለምን በነቢይነት እየመራ እንደሆነና በድንግል ማርያም ትዕዛዝና ምክር ዕለታዊ ድርጊቶቹን እንደሚፈጽም ይናገራል። የህመሙ መንስዔ ከ1972 እስከ 1974 ዓ.ም. ድረስ ዘወትር በየቀኑ ጫት አብዝቶ መቃሙ፣ ከጠዋት እስከ ማታ በውጪ ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍትን ማንበቡ፣ እንዲሁም በባዶ ቤት ብቻውን ማሳለፉ፣ አብዝቶ መበሳጨቱ፣ ክፉኛ እንቅልፍ ማጣቱና በገንዘብ እጦት ምክንያት ለጭንቀት መዳረጉ እንደነበር ግምቱን ያስቀምጣል። ድንግል ማርያም አዘዘችኝ በሚል ቆሻሻ ውሃ መጠጣት፣ በጎዳና ላይ እየሰገደ ረዥም መንገድ መጓዝ፣ ከሥራ ቦታው መጥፋትና ቤቱን ዘግቶ በረንዳ ማደር የተለመደ ተግባሩ ነበር። የተለያዩ የስለላ ድርጅቶች ሊመለምሉት ሴቶችን የሚልኩበት እየመሰለውና በከተማው ውስጥ የሚያያቸውን ሴቶች እንደፍቅረኛ እያሰበ ሲቀርብና ሲሸሽ ይታያል። በመጨረሻም ባልደረቦቹና ዘመዶቹ ሆስፒታል አስገብተውት በሕክምና ርዳታ ጤናው እንደተመለሰለት ይናገራል።

## ማንነት

ማኅበረሰብ በተለያዩ ማንነቶች በተዋቀሩ ቡድኖች የሚገነባ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ቡድን ወይም የማኅበረሰብ አካል የየራሱ ሚና ይኖረዋል። እንደ አንድ ማኅበራዊ ማንነት እብደትም የሚታወቅበት ልዩ ባህርያት አሉት። ማንነት ግለሰቡ ወይም ቡድኑ ለራሱ ከሚሰጠው ግምትና አተያይ ሊነሳ ወይም ከሌሎች አካላት ፍረጃ ሊመነጭ ይችላል። ከዚህ አኳያ የልቦለዱን ገጸ ባህርይ ማንነት ከራሱ እንደበት መተዋወቅ እንችላለን። የእብዱ ታሪክ የሚጀምርበት አንቀጽ እንዲህ የሚል ነው፤

*ህልም ማየት ስጀምር ነቢይ የሆንኩ መሰለኝ። ያለም ሕዝብ ሁሉ ለኔ ለኔ እያለ የሚሻማኝ መሰለኝ። ያለም ሕዝብ የሚመራው በኔ ህልም መሰለኝ። በተለይም አንድ ጓደኛዬ፣ “የግል ጸሐፊ አለችኝ። እኔ ሳረፍድ ትፈርምልኛለች። ባለጉዳዮችን ታስተናግድልኛለች። የምጽፈውን እያነበበች አስተያየት ትጽፍልኛለች። በዚህም ላይ ትወደኛለች ልክ እንደ ፍቅረኛዬ ናት። ትቀናለች፤ ታስቀናለች” ብሎ ከነገረኝ በኋላ አብራኝ ያለችዋ ልጅ በምስጢር የተቀጠረችልኝ ጸሐፊዬ መሰለችኝ። ከዚያች ዕለት በኋላ የግል ጸሐፊዬ የሆነች መሰለችኝ። (ገጽ 7)*

የስኪዞፍሬኒያ አንደኛው ባህርይ በሕልማለም መኖር እንደመሆኑ የባለታሪኩ ሕይወትም በዚሁ ሐሳብ ወለድ

ዓለም ውስጥ ራሱ በፈጠራቸውና ራሱን በሚያሞኝባቸው ገጠመኞችና ትርጉሞች ላይ የተመሠረተ አቅጣጫ ይዞ ይዘልቃል፡፡ ዳደኛው ያጫወተውንና ከጸሐፊው ጋር የመሠረተውን ቀረቤታ ወደራሱ በማምጣት አብራው የምትሠራውን ባልደረባውን ጸሐፊውና ፍቅረኛው አድርጎ የምር ይወስዳል፡፡ ይህም ራስን የማሞኘት የህመሙ አንደኛው መገለጫ ነው፡፡ ያልጠበቀቸው አቀራረብ የገጠማት ባልደረባው ደግሞ የምታሳየውን ምላሽ ምስጢራዊ ትርጉም እየፈጠረ ከራሱ ሐሳብ ጋር ለማስማማት ይሞክራል፡፡ እንድትጽፍለት የሰጣትን ጽሑፍ ሁለት ጊዜ ያህል ተባብራው ከተየበችለት በኋላ ፈቃደኛ ሳትሆን ስትቀር እምቢታዋን የወሰደው የጉዳዩን ምስጢራዊነት ይፋ እንዳይሆን ካደረገችው ጥንቃቄ አኳያ ነበር፡፡ ከዚችው ከበቡሽ ከተባለችው ባልደረባው ጋር በሰዎች መካከል በምስጢር ለማውራት በማሰብ የእጆቿን እንቅስቃሴ እንዳጠና ይገልጻል፡ ፡ በዚህም መሠረት የጽሑፍ መሰረዣ ቀለሟን የምታስቀምጥበትን ሁኔታ ተከታትሎ በማጥናት በሰጠው ትርጉም አንዱን ብልቃጥ ፊት ለፊት ስታቆመው ውጪ አንዲት ሴት ትጠብቅሃለች ማለት ነው ብሎ ተረጎመው፡፡ ብልቃጡን ስትፈነግለው ያቺ ሴት አመለጠችህ ማለቷ ነው ይላል፡፡ ሁለቱን ጎን ለጎን ስታቆማቸው ደግሞ አብረን እንሄዳለን ማለቷ ሲሆን፣ ላያቸው ላይ ጋዜጣ ከጫነችባቸው ሰወር ወዳለ ቦታ ልትወስደው እየጋበዘችው ይሆናል፡፡ አጠቃላይ የሕመም ወቅት ታሪኩ ይህን በመሰለ ሐሳብ ወለድ አቅጣጫ ላይ የሚዳዝ ነው፡፡ ለዚህም ነው የስኪዞፍሬኒያ ተጠቂ ይመስላል ያልኩት፡፡

ስኪዞፍሬኒያ ማለት በአስተሳሰብ መረበሽ ወይም መታወክ (ለምሳሌ ተጨባጭነት በሌላቸው ሐሳቦች ራስን ማሞኘት (delusions)፣ የአመለካከት ቅዠበት (በህልማለም መንጎድ (hallucinations))፣ የባህርይ መለወጥ (ቅጥ ያጣና የተዘበራረቀ ባህርይ ማሳየት)፣ ስሜታዊ ምላሽን ማጣት፣ መጠን ያለፈ ግድ የለሽነት፣ እንዲሁም በዕለታዊ ሕይወት ውስጥ በጉልህ በሚታይ ተግባርን ያለመፈጸም ችግር ዋና ዋና መገለጫዎቹ የሆነ የአእምሮ ሕመም ነው፡፡

ምልክቶቹም የተጠቂው ከእውነታ ጋር ራስን ማላመድ ወይም ማስታረቅ አለመቻል፣ ከሰበካው (ከማበራዊ ግንኙነቱ) መነጠል፣ ሐሳብንና ስሜትን ማቀናጀት ባለመቻል ተገቢ ያልሆኑ ስሜታዊ ምላሾችን መስጠት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የባህርይ መረበሹ ቢያንስ ስድስት ወራት የቆየና ዋና ዋናዎቹ የህመሙ ምልክቶችም ቢያንስ ለአንድ ወር ንቁ ሆነው መታየት እንዳለባቸው የአሜሪካ የአእምሮ ሕክምና ማኅበር ያስገነዝባል (American Psychiatric Association, 2000: 298)፡፡ ምንም እንኳ ስኪዞፍሬኒያ ሥነ ሕይወታዊና ማኅበረ ልቡናዊ (Psychosocial) መንስዔዎች ያሉት ቢሆንም ተጠኚው ልበለድ የሚዛመደው ከሁለተኛው ጎራ በመሆኑ በዚሁ ላይ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

ማኅበረ ልቡናዊ መንስዔዎች አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሆነው ለስኪዞፍሬኒያ መከሰት ሰበብ የሚሆኑ አካባቢያዊ ጫናዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ አካባቢያዊ መንስዔዎች መካከል መጠን ያለፈ የዕፅ ተጠቃሚነት፣ ማኅበራዊ መገለል፣ ስደት፣ የበዛ የከተሜነት ዘይቤ፣ ሥራ አጥነት፣ ፍቺ፣ በልጅነት የተፈጠረ አሰቃቂ ገጠመኝ፣ ወዘተ. ተጠቃሽ ናቸው (Fearon and Morgan, 2006)፡፡

በርግጥ የሕልማለም ሕይወቱና የገጠመኝ ትርጉሞቹ በአመዛኙ ተጠየቃዊነት ያላቸው ናቸው፡፡

*ትናንት አንድ ቡና ቤት ገባሁና እንዴት እንደምቀመጥ ግራ ገባኝ፡፡ ወደ ምስራቅ በግራ ልቀመጥ ብል የአሜሪካን ደጋፊ ልባል ነው፡፡ በቀኝ ብቀመጥ የኮሙኒስቶች ደጋፊ ብለው ሊጠሩኝ ነው፡፡ ወደ ሰሜን በቀኝ ልቀመጥ ብል ገንጣይ ልባል ሆነ፡፡ ዝም ብዬ መሀል ብቀመጥ መሀል ሰፋሪ ልባል ነው፡፡ እንዴት ማድረግ እንዳለብኝ ቆሜ ሳመነታ በዩ መጥቶ ወይ ተቀመጥ ወይ ውጣ አለኝ፡፡ በድፍረት ወደ ሰሜን ቁጭ አልኩ፡፡ (ገጽ 33)*

ይህ የአቅጣጫ ትእምርታዊ ትርጉም በርግጥም የፖለቲካ አስተሳሰብን ተከትሎ የሚሰነዘር በተጨባጩ ዓለም የሚታወቅ እውነታ ነው፡፡ የቀኝ እና የግራ ፖለቲካዊ አቋም የካፒታሊስትና የኮሙኒስት ርዕዮተ ዓለም መለያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ይህ ግንዛቤ የገጸ ባህርይውን ማኅበራዊ ዳራ የሚጠቁም ሲሆን፣ የአእምሮውን አሠራር ተጠየቃዊነት፣ የአስተሳሰቡን ፍሰት ተጨባጭነት፣ እንዲሁም በሕመሙ ውስጥም የአእምሮው ንቁነት እንዳልተለየው ያሳያል፡፡ ሐሳቡ ከሥፍራውና ከሁኔታው ጋር የማይገጥም መሆኑ ደግሞ የጤና ችግሩን ያረጋግጣል፡፡ ምንም እንኳ በባለታሪኩ አእምሮ ውስጥ የሚመላለሰውን ሐሳብ ሊረዳ የሚችልበት ዕድል ባይኖርም፣ የበዩ ማመናጨቅ የማኅበረሰቡን ምላሽ ይጠቁማል፡፡ ማኅበረሰቡ እብድ የሚለውን የራሱ አካል የሆነ ግለሰብ ማግለሉ፣ ዝቅ አድርጎ መመልከቱና ከሰብአዊ ክብሩ ማዋረዱ የተለመደ ይመስላል፡፡

ደራሲው የማኅበረሰብ መገልገያ በሆነ ተቋም ውስጥ የተፈጠረውን የገጸ ባህርይውን ግራ መጋባት (ማመንታት) በዚህ መልኩ የገለጸበት አንድምታዊ ትርጓሜ ይኖረው ይሆን? ጉዳዩ ቀላል የ"እብድ" ሐሳብ ብቻ ተደርጎ የሚታለፍ አይደለም፡፡ ይልቁንም ገጸ ባህርይው የኖረበትን ማኅበረ ፖለቲካዊ ቅኝትና የዘመኑን መንፈስ አመላካች ተደርጎ

ሊታሰብ ይችላል፡፡ ሰልፍን ማስተካከልን፣ የፖለቲካ አቋምን መወሰንንና ውግንናን መለየትን የግድ በሚለው ሶሻሊስት ኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ውስጥ ማንም ሰው እያንዳንዱን ርምጃ መዝኖ እና በጥንቃቄ ትርጉም ሰጥቶ መንቀሳቀስ ነበረበት፡፡ ይህን እውነታ ጥበባዊ ቀለም ሲሰጠው የገጸ ባህርይውን በነጻነት የማሰብ ሰብእና ተጠቅሟል፡፡ "እብድ" ስለሆነ ያሻውን የማሰብና የመናገር ነጻነቱን በሥነ ጽሑፋዊ መሣሪያነት ተጠቅሞ ትርጉሙ ብዙ የሆነውን የአቅጣጫ መረጣ ርዕሰ ነገር ማዕከላዊ ጉዳይ አድርጎታል፡፡ ምግብ ቤት የገባ ተገልጋይ በአንድ ጥግ ወይም አቅጣጫ መቀመጥ ያለበት መሆኑ አይቀሬ እውነታ ነው፡፡ ግን የቦታ ምርጫው የሚይዘው ትርጉም ደግሞ መንታ ይሆናል፡፡ የትም ቢቀመጥ ለውጥ እንደሌለው በሚታሰብበት አፍአዊ ትርጉሙ መቀመጫውን ለመምረጥ የገባበት ግራ መጋባት አስቂኝ ገጽታ አለው፡፡ በሌላ መልኩ ግን ሁሉም ትእምርታዊ ገጽታዎች ጠንካራ የፖለቲካ አቋም መመዘኛዎች ሆነው በሚተረጎሙበት የዘመኑ እውነታ የሕዝቡን ስቃይ፣ ስጋትና ግራ መጋባት አመላካች ሆኖ ሊታሰብ ይችላል፡፡

ስኪዞፍሬኒያ ከንቁ አእምሮ ቁጥጥር ውጪ በሕልም ዓለምና በሐሳብ ወለድ ትርጉም እየተገፉ ያልተለመዱ ተግባራትን የሚፈጽሙበት የቀውስ ሁኔታ በመሆኑ ከ"ጤነኞች" የሚያገኙት ምላሽ ይህንኑ የጤንነት ሁኔታ ያገናዘበ አይሆንም፡፡ እብዱ ገጸ ባህርይ በሐሳቡ የፈጠራት "ድንግል ማርያም" የሚላት ሴት እንደመራችው ከአውቶቡስ ተራ እስከ መሰለሚያ በዋናው ጎዳና ላይ እየሰገደ በመሄዱ ከተደጋጋሚ የመኪና አደጋ በአሽከርካሪዎቹ ብርታት ተርፏል፡፡ ይህቺው "እመቤቴ" የሚላት የምናብ አዛዡ ሌሊት ሰይጣኖች ሊያርዱት እንደመጡ እንደነገረችውና ተነስቶ ኡኡታውን እንዳቀለጠው ይናገራል፡፡ ቀን ጭቃ ላይ ተንከባለል እያለችው እንደሚንከባለልም ይገለጻል፡፡ ቆሻሻ ውሃ እንዲጠጣም እያዘዘችው ያለችውን ይፈጽማል፡፡ መንገዱ ላይ ሲንከባለል የሚመለከቱት ልጆች ሲከቡት በእመቤቱ ትዕዛዝ እያሳደደ ይመታቸዋል፡፡ በርና መስኮት በፍጥነት መክፈትና የመዝጋት ስልጠና ስትሰጠውም ጎረቤቶቹ እየተረበሹ ይጣሉታል፡፡ ቤቱን በውሃ እንዴት እንደሚያጸዳ ባስተማረችው መሠረት ውሃውን አብዝቶ ሲደፋው ምድር ላይ የሚኖሩ ጎረቤቶቹን ቤቶች ያዳርሳቸዋል፡፡ ለዚህ ምላሽ ሲሰጡት ደግሞ "ድንግል ማርያም" የሚላት አዛዡ አትፍራ ትለዋለች፡፡ ሰይጣኖች ስለሆኑ እስከመጨረሻው እንዲጋፈጣቸው ስለምትመክረው ይታገላቸዋል፡፡ ይህም አእምሮውን ሐሳብ ወለዱ የሕልም ዓለም የተቆጣጠረው መሆኑን ያሳያል፡፡

አንድ ቀን ወደማያውቀው ጸሎት ቤት ሄዶ በሴቶች መካከል በተቀመጠበት እጁን ለማሳረፍ ሲዘረጋው በአጋጣሚ በአንዲት ሴት ጭኖች መካከል ያርፋል፡፡ እጁን እየሞቀው ሴትዮዋም ጭኗን ለማላቀቅ ፍላጎት ሳታሳይ በመቆየታቸው የተሰብሳቢዎቹን ግልምጫና ጡጫ ይቀምሳሉ፡፡ ይህን አጋጣሚ የሚተረጉመው ራሱንና ባለጭኗን ሴት "ሁለት ምስኪን ሰማእታት" በሚል ፍረጃ ነው፡፡

*ሰማእት የሚለው ቃል በአንድ አጭር ልቦለድ ውስጥ ያነበብኩትን የአንድ ሰማእት ታሪክ አስታወሰኝ፡፡ አንድ ጃፓናዊ አንዲት ልጅ አስረግዘሃል ብለው የመንደሩ ሰዎች በሳት ያቃጥሉታል፡፡ ከልጅቷ ጋር ብዙ ጊዜ ታይቶ ስለነበር ነው፡፡*

*ሴቶች እሳት ናቸው፡፡ እኛ የሳት እራት ነን፡፡ ብርሃናቸው ስቦን ስንጠጋ ተቃጥለን እናልቃለን፡፡ ይኸው አሁን እኔን አቃጠለችኝ አይደል? (ገጽ 31)*

የአእምሮው የሀሳብ ቅኝት በአንድ በኩል ያልረጋና ከአንድ ሐሳብ ወደ ሌላ የሚረግጥ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ ከሰከነ አእምሮ የሚፈልቅ የንቁ አእምሮ ሀሳብም ይታይበታል፡፡ ይህም የአእምሮ ጤና ችግር አእምሮን ፍጹም ማጣት ወይም ሌላ ማንነት የሚፈጠርበት ሳይሆን በጤናማ አእምሮውና በሕመሙ መካከል የሚፈራረቅ የአስተሳሰብ ቅጥ ያለ ይመስላል፡፡ የ"ሁለት ምስኪን ሰማእታት" ፍረጃው ከእውነታው የማይገጥምና በጸሎት ቤት ውስጥ ጾታዊ (ወሲባዊ) ንክኪ የሚወገዝበት ሆኖ ሳለ የሰማእትነት ምስል መፍጠሩ ስለሚቃረን ከአእምሮ ሕመምተኛ የሚጠበቅ አገላለጽ ነው፡፡ ሆኖም ሰማእትነትን ካነበበው አጭር ልቦለድ ታሪክ ጋር ያዛመደበት ሁኔታ፣ ይልቁንም ተዛምዶውን የፈከረበት መንገድ የአእምሮን ንቃት የሚጠይቅ በመሆኑ በደፈናው "የእብድ ሐሳብ" ሊባል አይችልም፡፡ የጃፓናዊውን በእሳት መቃጠል ከሴቶች የእሳትነት ባህርይ ጋር ያዛምድና ራሱንና የጾታ አጋሮቹን የእሳት ራት በማድረግ አሁን ሰለባ ከሆነበት አጋጣሚ ጋር ግሩም አድርጎ ማቆራኘቱ የአእምሮውን ንቃት የሚሳይ ነው፡፡ ይህም የአእምሮ ሕመምን በደፈናው አንድና ተመሳሳይ አድርጎ በማሰብ አእምሮውን ያጣ፣ ከሰውነት የወረደና የማያስብ ተደርጎ የተመሠረተውን የልማድ ፍረጃ (Stereotype) ጥያቄ ውስጥ የሚከት ነው፡፡

አብዛኛው የአእምሮ ሕሙማን ድርጊት በ"ጤነኞቹ" ዘንድ የሚሰጠው ትርጉም የድርጊቱ ፈጻሚዎች ከሚሰማቸውና ከሚያስቡት የሚቃረን በመሆኑ የአተረጓጎምና የአረዳድ ልዩነት መኖሩን ማስተዋል ይቻላል፡፡ በእብዱ ልቦለድ ውስጥ እንደምንመለከተው ገጸ ባህርይው በ"ድንግል ማርያም" ትዕዛዝ ሥር ሆኖ የሚፈጽማቸው ድርጊቶች ከእሱ

ቁጥጥር ውጪ የሚከናወኑ መሆናቸውን በዙሪያው ያሉ ሰዎች አያውቁለትም። ውሃ የሚደፉባቸው ጎረቤቶቹ እንዲያቆምላቸው ሲጠይቁት ሰይጣኖች በመሆናቸው ሊታገላቸው እንደሚገባ ይታዘዛል። ጭቃ ላይ ሲንከባለል የሚከቡትን ልጆች ለካራቴ ስልጠናው እንዲለማመድባቸው ስለምትመክረው እያሳደደ ይደበድባቸዋል።

በሌሎቹ አካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሰው ማግለል፣ አድልኦና ጥቃት በአእምሮ ሕሙማን ላይ ገዝፎ መታየቱ የተለመደ ነው። የማኅበራዊ ጫናው መንስዔ በልማዱ የተዘወተሩ ደንቦችን (Norms)፣ ማለትም መልበስ (እርቃን አለመውጣት)፣ እንደፈለጉ አለመናገር ወይም ከብቻ ንግግር መቆጠብ፣ ይሉኝታና አክብሮትን የመሳሰሉ ማኅበራዊ ሥርዓቶችን መጣስ የሚያስከትለው ውጤት ሊሆን ይችላል። ከደንቦቹ ያፈነገጠውን ማግለልና ማጥቃት ማኅበራዊ ሥርዓቱ የሚጠበቅበት ስልት ይሆንና የአእምሮ ሕሙማኑ ሰለባ ይሆናሉ። ለዚህም ነው ከሌሎች አካል ጉዳተኞች ጋር ሲነጻጸር የአእምሮ ጤና ችግር ያለባቸውን ባእድ አድርጎ ማሰብና ጥቃት ማድረሱ ከፍ የሚለው። "እብድ" በባህሉ መጠጊያና አጋዥ የሌለው በመሆኑ ለጥቃት የተጋለጠ ነው። ማንም እብድን ስላጠቃ ለውግዘት አይበቃም። እብድን መማታት፣ ማሳደድ፣ ውሃ መርጨት፣ መሳደብ፣ ወዘተ. እንደነውር አይቆጠርም። "ለእኔ ቢጤ" የሚመጸውተው ምእመን ለእብድ ግን አንድ ብርጭቆ ውሃ ይነፍጋል። እብድ የጠጣበትን ወይም የበላበትን ዕቃም የረከሰ ይመስል መጸየፍ የተለመደ ነው። ምንም እንኳ ተንኳሽ የሆኑ የአእምሮ ሕሙማን ቢኖሩም፣ ሁሉንም በጅምላ አስፈሪ፣ ጨካኝና አደገኛ አድርጎ ማሰቡ ማኅበራዊ ስምምነት ያለው ይመስላል።

**የኃይል ግንኙነት**

አካል ጉዳተኛነት፣ በተለይም የአእምሮ አካል ጉዳተኛነት በማኅበረሰብ ውስጥ ያለው አቀባበልና የኃይል ግንኙነት በአመዛኙ ሚዛኑን የሳተ ወይም የተዛባ ነው። በዚህ ልቦለድ ውስጥም እብዱ ገጸ ባህርይ በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለው ሥፍራ የተናቀ፣ የተጠላና የተዘነጋ መሆኑን የሚጠቁሙ የተወሰኑ አጋጣሚዎችን መጥቀስ ይቻላል። ከሆስፒታል ድኖ እንደወጣ ወደ ሥራ እንዳይመለስ መከልከሉ አንደኛው መጥፎ አጋጣሚ ነው። ምንም እንኳ ሙሉ ጤነኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ በሐኪሙ አስጽፎ ለመሥሪያ ቤቱ ቢያቀርብም ወደ ሥራው እንዳይመለስ ተደርጓል። ይህ ደግሞ የጤና ችግሩ በሕክምና የሚድን ተደርጎ ከመወሰድ ይልቅ ጤነኛም ሆኖ ለመገለል እንዳበቃው የሚያመለክት ነው። ከዚሁ የሥራ ስንብቱ ጋር የሚያያዘውንና ከገጠር አምጥቶ አብራው እንድትኖር ያደረጋት ሚስቱ ጸሐይ የምታደርግለትን የሞራል ድጋፍ እንመልከት፤

*እንደ ጸሐይ መሳም የሚወድ ሰው የለም። ከየት እንደተማረችው አላውቅም። ደርሰ እቅፍ ታደርግና ከንፈሬን ትስመኛለች። መናቅ ወይም መጸየፍ የሚባል ነገር የለም። ‹አይቾ! አይዬቾዬ!› ትልና ጥምጥም ትልብኛለች። ያኔ ገና እብድ እያለሁ እንኳ ‹አንቺ ይገድልሻል ወዲያ ትተሸው ሒጂ› እያሉ ሲመክሯት እምቢ ነው ያለች። ከዳንኩ በኋላም መሥሪያ ቤቱ ወደ ሥራህ አንመልስህም ብሎ ሲከለክለኝ ‹ተወው አብሬህ እቸገራለሁ› አለች። (ገጽ 70)*

ከዚህ ጥቅስ የሚመዘዙ ሦስት ነጥቦች የአካል ጉዳተኛነትን የኃይል ግንኙነት ሊያስረዱ ይችላሉ። የመጀመሪያው "መናቅ ወይም መጸየፍ የሚባል ነገር የለም" የሚለው ዐረፍተ ነገር ነው። በባልና ሚስት መካከል ባለ የፍቅር ተራክቦ ንቀትና መጸየፍ የሚጠበቅ አይደለም፤ በራሷ ፈቃድ፣ በራሷ ጉትጎታና ተጽዕኖ ከጎጃም ድረስ መጥታ ባልነቱን ተቀብላ አብራው ስትኖር የንቀትንና ጽዩፍነትን ድንበር ተሻግራዋለች ብልን ብንገምት ስህተት አይሆንም። በዚህም ምክንያት ባልነቱ ወይም ፍቅረኛነቱ ንቀትንና መጸየፍን የሚያሳስብ መንስዔ አይሆንም ማለት ነው። ቀሪው ነገር የአእምሮ ጤና ችግሩና እሱን ተከትሎ የመጣው አካል ጉዳተኛነት ይሆናል። እሱም ቢሆን በእሷ አእምሮ ውስጥ የታሰበ ሳይሆን ስሜቱ የመነጨው ከራሱ ከአካል ጉዳተኛው ነው። እንደማትንቀውና እንደማትጸየፈው የሚነግረን ራሱ ነውና። ይህም የማኅበራዊ መገለልና ጥቃት መገለጫ የሆነው የግለሰቡ ስሜት "እናቃለሁ"፣ "ይጸየፉኛል" የሚል ጠንካራ ፍርሃትና ስጋት የተጫነው መሆኑን ያሳየናል። እንደማኅረሰብ አባልነቱ ከውጪ ሊገጥመው የሚችለውን ጫና የተረዳ፣ በዚያውም የራሱን ማኅበራዊ ሥፍራ የወሰነ ሆኖ እናገኘዋለን።

ሁለተኛው ነጥብ "ያኔ ገና እብድ እያለሁ እንኳ ‹አንቺ ይገድልሻል ወዲያ ትተሸው ሒጂ› እያሉ ሲመክሯት ‹እምቢ› ነው ያለች" በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ይገኛል። ይህ የተራኪው ገለጻ የማኅበረሰቡን አመለካከትና አረዳድ ያሳያል፡ ፡ መካሪዋ አንድ ሰው አይደለም፤ በብዙ ቁጥር የተገለጸ በመሆኑ የተወሰነ የማኅበረሰብ ቡድን (የማኅበረሰቡ ማሳያ) ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ማኅበረሰቡ "እብደት"ን የሚረዳው እንደ አንድ የጤና ችግር አይደለም። ይልቁንም አጥፊ፣ የማያስብና አስፈሪ አድርጎ የራሱን ፍረጃ ፈጥሯል። በመሆኑም በዚህ ዐውድ ለተጠቂው ገጸ ባህርይ የሰጠው ማኅበራዊ ሥፍራ "ገዳይ" አድርጎ ነው። ትታው እንድትሄድ የቀረበው ምክረ ሐሳብም ግለሰቡን ከማኅበረሰብ የሚነጥልና ብቻውን የሚያስቀር፣ የሚያገልልና ባይተዋር

የሚያደርግ ነው። በአካል ጉዳተኛ ገጸ ባሕርያት ጥናት ላይ ተመሥርቶ የሕጻናት ሥነ ጽሑፍን የመረመሩት Goldman (1990) ይህንኑ እውነታ በሚያጠናክር መልኩ እንደጠቆሙት በሕጻናት ሥነ ጽሑፍ ውስጥ የቀረበ ማናቸውም ስነት ወይም የአካል ጉዳት አስተማስሎው እኩይነት ወይም አጥፊነት ነው። (ገጽ 1)

ሦስተኛው ነጥብ ደግሞ "ከዳንኩ በኋላም መሥሪያ ቤቴ ወደ ሥራህ አንመልስህም ብሎ ሲከለክለኝ" በሚለው ሐረግ ውስጥ ይገኛል። ማኅበረሰቡ በልማድ ብቻ አይደለም የአእምሮ ጤና ስነትን የሚጸየፈው። ለዚህ የጤና ችግር የሚሰጠው አሉታዊ ትርጉምና የመረረ ርምጃ ተቋማዊ ገጽታም ይዟል። ግለሰቡ ከጤና ችግሩ ሙሉ በሙሉ ተላቅቆ ለሥራ ብቁ መሆኑን የሐኪም ማረጋገጫ ቢያቀርብም መሥሪያ ቤቱ ግን ወደ ሥራው እንዳይመለስ ከልክሎታል። ይህ ክልከላ አካል ጉዳተኛነት የተቀናጀ የማኅበረሰብ ጥቃት የሚያርፍበትና ከጤና ችግርነት አልፎ የሚሄድ ማኅበራዊ ገጽታ እንዳለው ያመላክታል።

የአእምሯዊ አካል ጉዳተኛነት ማኅበራዊ አቀባበል አሉታዊነት በሌሎች የትረካው ክፍሎችም ይታያል። ቀጥሎ የቀረበው አጋጣሚም ምሳሌ ሊሆን የሚችልነው። ባለታሪኩ በጎዳና ላይ በሚጓዝበት በአንድ አጋጣሚ የአብዮት ጠባቂዎች አስቁመው ወዴት እንደሚሄድ ይጠይቁታል። መልስ ይሰጣቸውና መንገዱን ሲቀጥል ፖሊሶች ያያል። አሁንም መጠየቅና ምናልባትም መታሠር ሊኖር እንደሚችል በመፍራት መንገድ ቀይሮ በመንደር ውስጥ በሱቆች መካከል ሲጓዝ ዘበኞች አባርረው በመያዝ "ዱላቸው እስኪሰበር ቀጠቀጡኝ" ይላል። *"እየተመታሁ ሮጥኩ። ከተዉኝ በኋላ ተጸጽተው አባረሩኝ። አትክልት ተራ አጠገብ ደረሱብኝና ግንብ አስጠግተው እንደእብድ ውሻ ቀጠቀጡኝ"* (ገጽ 44)። እነዚህ ዘበኞች ሲሰርቅ ይዘውት ወይም ሌላ የአምባጓሮ ችግር ስለፈጠረ አልነበረም የቀጠቀጡት። ያለምንም ምክንያት ነው ዱላቸው እስኪሰበር በጭካኔ የደበደቡት። በተጸጸቱበት ጊዜም አባረው ይዘው በበለጠ ጭካኔ ደበደቡት እንጂ አላዘኑለትም። ከዚህ ድብደባ ተርፎ መንገዱን ሲቀጥል የፈራው አልቀረም ፖሊሶች ያዙት። ስሙንና አድራሻውን ከጠየቁት በኋላ ግን "አቡነ ዘበሰማያት"ን እንዲደግም ነበር የጠየቁት። ደግሞ ሲጨርስ፣ "ጎበዝ ከመታችሁኝ በዱላ አትምቱኝ። በጥይት ግደሉኝ" አላቸውና ግድግዳ ተደግፎ ተመቻቸላቸው። ሆኖም ሳይገድሉ ለቀቁትና ሌሎች ፖሊሶች ይዘው እስር ቤት ወረወሩት።

ፖሊሶቹም ሆኑ ዘበኞቹ የአካባቢን ሰላም የማስከበርና የዜጋውን ደኅንነት የማስጠበቅ ተልዕኮ ያላቸው ቢሆኑም እንዲጠብቁት ኃላፊነት የተጣለባቸውን ዜጋ ያለአንዳች ምክንያት በጭካኔ ሲያሰቃዩ ይታያሉ። ምንም እንኳ ዘመኑ የነጻ ርምጃ አዋጅ ማግስት እንደመሆኑ የፖሊሶቹና አብዮት ጥበቃዎቹ ርምጃ ተጠያቂነት የሌለው ቢሆንም፣ ግለሰቡ ከማናቸውም የፖለቲካ ፍላጎትና አመለካከት የሚመነጭ እንዳልሆነ ለመረዳት አያዳግትም። ራሱን መከላከል የማይችል፣ ክስ መስርቶ በሕግ መብቱን የማያስከብር፣ ደካማና የወገኖቹ እገዛ የሚያስፈልገው ዜጋ ቢሆንም ያለ ምንም ጥፋት የዱላና የእስር ሰለባ ተደርጓል። የአጥቂዎቹ ድርጊት የሕግም ሆነ የሞራል ኃላፊነት የሚያስከትል፣ የግፍ ተግባር ቢሆንም የተጠለሉት የማኅበረሰባቸውን የባህል ይሁንታና ማኅበራዊ ቸልታ ነው። በዚህም ምክንያት የሚከሳቸው፣ የሚወቅሳቸው የለም። የህግ አስከባሪዎቹ የማን አለብኝ ድርጊት ከኃላፊነት ወሰናቸው አልፎ ከጉዳዩ ጋር የማይገናኝ ጥያቄ በማቅረብ አቡነ ዘበሰማያት እንዲደግም ባዘዙበት ሁኔታ ይገለጻል። ባለታሪኩ የቤተ ክህነት ሰው ነኝ ብሎ ሊያጭበረብር የሞከረበት ሁኔታ በሌለበት ደርሰው አቡነ ዘበሰማያት እንዲደግም መጠየቃቸው ምናልባትም "እብዱ ማነው?" ያሰኛል። አልፎ ሂያጅን በዱላ የሚያንቆራጥጡት ዘበኞች ድርጊትም ከዚሁ ጥያቄ የማያልፍ ነው። ምክንያቱም የአእምሮ ሕመምተኛነት ወንጀል አይደለም፤ ለነገሩ ወንጀለኛም ያለፍርድ ይደብደብ የሚል ደንብ የለም። ማንም ግን የአእምሮ ጤና ችግር ያለበትን ግለሰብ ቢያጠቃና ቢያንቋሽሽ ወይም ማናቸውንም በደል ቢያደርስበት ተጠያቂነት የለበትም። የአእምሮ ጤና ችግር ያለባቸው አካል ጉዳተኞች በሌሎቹ ስነቶች አካል ጉዳተኛ ከሆኑት ይልቅ ይበልጥ ለጭቆና፣ ለአድልኦና መገለል ተጋላጭ ናቸው ሲባልም ይህ ማለት ነው፡ ፡

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ይዟቸው የተነሳው ሁለት ነጥቦች "እብድ" ማነው? በማኅበራዊ መስተጋብሩ ውስጥ ያለው አቀባበልና ሥፍራ ምን ይመስላል? የሚሉት ናቸው። "እብደት" የአእምሮ ጤና ችግር በመሆኑ እንደሌላው ሰብአዊ ፍጡር ሁሉ ሙሉ አካልነቱ ጥያቄ ውስጥ አይገባም። የአእምሮ አሠራሩ ግን "ጤናማ" ሰው ከሚፈጽማቸው ተግባራትና ከሚያሳያቸው ባህርያት የተለዩ እንግዳ እንቅስቃሴዎች ወይም ድርጊቶች ሲሆኑ ያስገምቱታል። የ"እብዱ" ገጸ ባህርይ እንግዳ ተግባራት የጎርፍ ውሃ መጠጣት፣ ጎዳና ላይ እየሰገዱ መጓዝ፣ ከሴቶች ጋር የሚያደርገውን ወይይት ሌላ አቅጣጫ ማስያዝና መሰል ድርጊቶቹ ናቸው። እነዚህ "ጤናማ" ሰው ከሚያደርገው የተለዩ ተግባራት የተለየ

ማንነት አሰጥተውታል።

ከእነዚህ ድርጊቶቹ ባሻገር ግን በመደበኛነት አእምሮው የሚያሰላስለበት ስልት እንደሌላው ሰው ሁሉ ተጠየቃዊነት ያለው፣ ነገሮችን የሚረዳበት መንገድም ምክንያታዊ የሆነ ነው። በዘፈቀደ ወይም ያለምክንያት የሚፈጽመው ተግባር የለም። ያስባል፤ ያሰላስላል፤ ያዘምዳል፤ ትርጉም ይሰጣል። አእምሮ የሚሠራውን ተግባር ሁሉ የእሱ አእምሮም ይሠራዋል። የሚያስብበት መንገድ ከ"ጤነኛው" ሰው ያልተለየ ሆኖ የሚያስበው ነገር ወይም ሐሳቡ የሚመሠረትበት ውቅርና የሚመራበት ቅጥ ግን ይለያል። የጎርፍ ውሃ የሚጠጣበትም ሆነ ጎዳና ላይ እየሠገደ የሚጓዝበት ስውር አእምሯዊ ምክንያት አለው።

ይሁንና በጥቅሉ የገጸ ባህርይውን የጤና ችግር አስመልክቶ የተያዘው ማኅበራዊ አረዳድ ከእውነታው የተለጠጠና የተጋነነ ነው። ጉዳዩን እንደ አንድ የጤና ችግር ከማየት ይልቅ ቋሚ (የማይድን) አድርጎ በመገንዘብ የጤና ችግሩ ሲወገድም ቀድሞ የተያዘው የማግለልና የጥቃት አቀባበል ቀጥሏል። ማኅበራዊ ጥቃቱ ከግለሰብ ወደ ቡድንና ተቋም እያደገ የሚሄድ ትስስር ያለው በመሆኑ በአካል ጉዳተኛነት ትርጉም ላይ እንደተገለጸው የተቀናጀ የማኅበረሰባዊ ጥቃት ዒላማ ሆኗል ብሎ መደምደም ይቻላል።

የአእምሮ ሕመም ያገኘው ማኅበራዊ አቀባበል በእውነታ ላይ ያልተመሠረተ፣ በጅምላ ፍረጃ ላይ የቆመ፣ ማግለል፣ ጥላቻና ጥቃት ጎልቶ የሚታይበት መሆኑን የመጽሐፉ ታሪክ ያስረዳል። የአእምሮ ሕሙማንን በጅምላ ተንኳሽ፣ አጥቂና አጥፊ አድርጎ ማሰብ፣ አእምራቸውን ሙሉ በሙሉ እንዳጡና ሰብአዊ ባህርይ እንደሌላቸው መገመት፣ እንዲሁም የጤና ችግሩ ሊድን ወይም ሊታከም የማይችል የኃጢአትና ርግማን ውጤት እንደሆነ ማመን ከ"ደህነኛው" ኅብረተሰብ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የተዘባ እንዲሆን አድርጎታል። የስኪዞፍሬኒያ ተጠቂ የሆነው የእብዱ ገጸባህርይ ያለአንዳች ጥፋትና የወንጀል ድርጊት ለድብደባ፣ ለእንግልትና ለእስር ተዳርጓል። ጥቃት የተፈጸመበት ደግሞ የዜጎችን ደኅንነት እንዲጠብቁ ኃላፊነት ባለባቸው ፖሊሶችና የጥበቃ አባላት ነው። የሕግ አስከባሪዎቹ ድርጊት "እብደት" ያገኘውን ማኅበራዊ አቀባበል በሚገባ ያስረዳል። ማንም "እብድ"ን ቢደበድብ፣ ቢያስር፣ ቢያንገላታ የሕግም ሆነ የሞራል ተጠያቂነት እንደሌለበት ማኅበረሰቡ ይሁነኝ ብሎ የተቀበለው ደንብ ይመስላል። ይህም የአእምሮ ጤና ስነት የተራቆተ ማኅበራዊ ማንነት፣ ከሰብአዊ ክብር የወረደ ምስል ይዞ የቀረበ መሆኑን ያሳያል። አካል ጉዳተኛነት እንደማንነት በማኅበረሰብ ውስጥ ያለው ሚና ጭቆና፣ ውርደት፣ መገለልና የጥቃት ሰለባነት ሆኖ ተስተማስሏል ማለት ይቻላል።

## ዋቢ መጻሕፍትና ጥናቶች


**ቀዳማይ ምንጭ**

አውግቸው ተረፈ። (2002)። *እብዱ*። አዲስ አበባ፤ ፋር ኢስት ትሬዲንግ።

**ካልአይ ምንጮች**

Alemu, A. (2014). *Challenges of teaching writing skills in Ethiopian universities*. Unpublished master's thesis, Addis Ababa University, Addis Ababa, Ethiopia.

ቴዎድሮስ ገብሬ። (2001 ዓ.ም)። (2ኛ ዕትም) *በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ።* አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ፣

አምሳሉ አክሊሉ። (1976 ዓ.ም)። *"አጭር የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ቅኝት።"* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ያልታተመ።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። (1948)። *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ደስታ ተክለ ወልድ። (1962)። *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

Alemu, A. (2014). Challenges of teaching writing skills in Ethiopian universities. Unpublished master's thesis, Addis Ababa University, Addis Ababa, Ethiopia.Beauvoir, S. (1989). The Second Sex. New York: Vintage.

Bérubé, M. (2005). "Disability and Narrative." PMLA 120.2: 568–576.

Davis, J. (2002). Bending over Backwards: Disability, Dismodernism & Other Difficult Positions. New York: New York University Press.

Donaldson, J. (2018). Literature of madness Disability studies and Mental Health. New York: Macmillan

Foucault, M. (1978). The History of Sexuality, Vol. 1, trans. Robert Hurley. New York: Vintage.

Gaventa, J. (2003) Power after Lukes: a review of the literature, Brighton: Institute of Development Studies. http://www.powercube.net.

Goffman, E. (1963). Stigma: Notes on the Management of Spoiled Identity. New York: Simon and Schuster.

Goldman, L. (1990). "The portrayal of physically disabled children in realistic fiction since 1975".

(unpublished master's thesis). University of Wyoming, Laramie.

Hall, A. (2016). Literature and Disability. London: Routledge.

Kelly, M. (2009). The Political Philosophy of Michel Foucault. http://www.ResearchGate.net/publications

Linton, S. (1998). Claiming Disability: Knowledge and Identity. New York: New York University Press.

Shakespeare, T. "The Social Model of Disability." In The Disability Studies Reader, ed. Lennard J. Davis, 197–204. New York: Routledge. (2006.)

Siebers, T. (2008). Disability Theory. USA: The University of Michigan Press.

Tirusew Teferra. (2022). Disability in Ethiopia: Issues, Imsights and Implications. (2nd Ed.) Addis Ababa: Addis Ababa University Press.

Van Dijk, T. A. (1995) Discourse analysis as ideology analysis in Christina Schaffer and Anita L. Wenden (eds.) Language and peace. Dartmouth Aldershot.